የሰ/መ/ቁ. 154213

ሐምሌ 17 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳባ መስፍን ከጠበቃቸው አቶ እዩኤል ጄሬኔ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ንጋቱ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ከሳሽ በቀን 08/07/2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ያለው ጋብቻ በፍርድ ቤት በኩል እንዲፈርስና የፍቺ ውጤት የሆነው የጋራ ንብረቶች ናቸው ያሉትን ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ድረስ ዘርዝረው አቅርበዋልለ፡፡

ተጠሪ /የስር ተከሳሽ/ 7/09/2009 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልሳቸው ከአመልካች /ከስር ከሳሽ/ ጋር ጋብቻ የፈጸሙት ሐምሌ 16 ቀን 1997 ዓ/ም መሆኑን ገልጸው አመልካች ካቀረቡት ንብረቶች መካከል ባህር ዳር ከተማ ያለውን ቤት ከጋብቻ በፊት የሠሩት የግል ንብረታቸው እንደሆነ ከቁጠባ ማህበር በብድር የወሰዱትን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለትዳር ጥቅም ያዋሉ መሆኑን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለያዩ ቅርንጫፎች ያለውን ገንዘብ በተመለከተ የግል እና የጋራ ነው ያሉትን ዘርዝረው ያቀረቡ ሲሆን ሌሎች ንብረቶችንም በተመለከተ የጋራ ነው ያሉዋቸውን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የግራ ቀኙን ምስክሮችን ቃል ሰምቶ የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ እንዲሁም ከተለያዩ አካላት መግላጫዎችን ጠይቆ እንዲቀርቡ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ

1. በህብር ስኳር አክሲዮን ማህበር በተጠሪ ስም ያሉ 2 አክስዮን ብር 2,000 /ሁለት ሺህ/ ግምት ያለው የጋራ ነው እኩል ይካፈሉ የትርፍ ክፍፍል ተደርጎ እንደማይታወቅ የተገለጸ በመሆኑ ክፍፍል እስኪደረግ ድረስ ያለው የትርፍ ክፍፍል ግማሽ የአመልካች ድርሻ በመሆኑ ታስቦ እንዲከፈላቸው።
2. ባበህርዳር ከተማ ቀበሌ 14 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው እና በተጠሪ ስም የተመዘገባው ቤት ከትዳር በፊት የተፈራ በመሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ነው።
3. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደንግላ ቅርንጫፍ በተጠሪ ስም ያለው ብር 1,355 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ አምስት/ ባህርዳር ቅርንጫፍ በተጠሪ ስም የሚገኘው ብር 21 /ሃያ አንድ/ በስላሴ ቅርንጫፍ አዲስ አበባ ንግድ ባንክ በተጠሪ ስም የሚገኘው ብር 340 /ሶስት መቶ አርባ/ በልደታ ቅርንጫፍ አዲስ አበባ ንግድ ባንክ በተጠሪ ስም የሚገኘው ብር 31.20 /ሰላሳ አንድ ብር ከሃያ ሳንቲም/ ተጠሪ ለአምልካች ሊያካፈል ይገባል።
4. በስላሴ ቅርንጫፍ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብር 290,889.20 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሃያ ሳንቲም/ ተጠሪ ከፍቺ በኃላ ገቢ ያደረጉ ወይም ያስቀመጡ ስለሆነ ለአመልካች አይገባቸውም።
5. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሠራተኞች ብድርና ቁጠባ ሕብረት ስራ ማሕበር ውስጥ በተጠሪ ስም እስከ ሀምሌ ወር 2005 ዓ/ም ያለ ተቀማጭ ብር 20,210.96 /ሃያ ሺህ ሁለት መቶ አስር ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/ ላይ ግማሽ ድርሻ የአመልካች መሆኑ ተረጋግጧል። ከ2005 ዓ/ም ትርፍ ክፍፍል ብር 700 ውስጥ ብር 350 /ሶስት መቶ ሃምሳ ብር/ የአመልካች ድርሻ ስለሆነ እንዲከፈላቸው በተቀማጩ ገንዘብ ልክ ክፍፍል እስኪደርግ ያለ የትርፍ ክፍፍል ካለም ግማሹ ለአመልካች እንዲካፍል።
6. በ2004 ዓ/ም ከተቋሙ ብድር ተወስዶ ቀሪ እዳ ብር 19,540 /አስራ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ አርባ/ መኖሩ ስለተረጋገጠ ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ።
7. የተዘራዘሩትን የቤት ቁሳቁሶችን እኩል እንዲካፈሉ።
8. አመልካች ብር 5,000 /አምስት ሺህ / ለትዳር ጥቅም ተበድሬአለሁ ቢሉም በማስረጃ ያልረጋገጠ በመሆኑ ታልፏል ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

የአሁን አመልካች ከተሰጠው ውሳኔ መካከል ቅር የተሰኙባቸውን 1ኛ/ ባህር ዳር ከተማ ያለው ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው መባሉን 2ኛ/ ተጠሪ ከአመልካች እውቅና ውጪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሠራተኞች ብድርና ቁጠባ ሕብረት ስራ ማህበር የተበደሩትን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ በሚመለከት 3ኛ/ ስላሴ ቅርንጫፍ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚገኘው ገንዘብ የተጠሪ ብቻ ነው መባሉን በመቃወም 4ኛ/ የስር ፍርድ ቤት አንድ ኪቼን ካቢኔት አንድ ቁም ሳጥን እና አንድ አልጋ በተመለከተ በፍርዱ ላይ የጋራ ነው ካለ በኋላ በውሳኔው አላካተተም በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱትን የቅሬታ ነጥቦችን ባለመቀበል በአራተኛው የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ ላይ መልስ ሰጪ /የአሁን ተጠሪ/ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ ከተራ ቁጥር 1 ኛ እስከ 3 ኛ ድረስ ተጠቅሰው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረቡትን ቅሬታዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን የቅሬታ ነጥቦች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የጉዳዩ አከራካሪ የሆነው ቤት የመስሪያ ፈቃድ የተሰጠው ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ተሰርቶ ተጠናቀቀ የሚባለው በጋብቻ ውስጥ ወይም ወጭ መሆኑ ባልተረጋገጠበት የተጠሪ ነው የተባለበት ተጠሪ አመልካች ሳያውቁ የተበደሩት ብድር እዳ  የጋራ የተባለበትና ተጠሪ በውጭ በነበሩበት ጊዜ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ከፍቺ በኃላ ወደ እራሳቸው ሂሳብ ያስገቡት ገንዘብ የተጠሪ የግሉ ነው የተባለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል በቀን 18/08/2010 ዓ/ም በተፃፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ግንቦት 9 ቀን 2010 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቦአል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳይ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 16 ቀን 1997 ዓ/ም ጋብቻ መፈጸማቸው እንዲሁም በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰ ሀምሌ 1 ቀን 2005 ዓ/ም መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው የጋብቻ ውጤት የሆኑት ንብረቶች ሲሆን የመጀመሪያው በባህዳር ከተማ ቀበሌ 14 የቤት ቁጥር አዳስ የሆነው እና በአሁን ተጠሪ ስም የተመዘገበው ቤት ነው፡፡ ይህን ቤት አመልካች በትዳር ውስጥ የተሰራ ስለሆነ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት በመሆኑ ድርሻዬ ይገባኛል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከትዳር በፊት የተፈራ በመሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ቤቱ በትዳር ውስጥ የተፈራ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው ወይስ የተጠሪ የግል ንብረት ነው? የሚለው በጥልቀት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የሰው ምስክሮች ከመስማቱም ባሻገር የሰነድ ማስረጃዎችን እንደተመለከተ ከውሳኔው የተመለከትን ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በተለይም አመልካች ያቀረቡዋቸውን የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ከተለያዩ አካላት የተላኩትን ወይም የቀረቡትን የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን በአግባቡ ተመለክቷል ወይ? አመልካች ያቀረቡዋቸውን እንዲሁም ከተለያዩ አካላት የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ሁሉንም በውሳኔው ላይ አሰፍሯል ወይም ያልተቀበለበትን ምክንያት ተችሏል ወይ? ግልጽነት የጎደለው ማስረጃ ሲቀርብ ለትክክለኛ ፍርድ ሲባል ስለማስረጃው መግለጫ የሰጠውን አካል ፍርድ ቤቱ አመቺ ነው ባለው መንገድ ማጣራት አልነበረበትም ወይ? የሚሉትን ይህ ችሎት በጥልቀት ተመልክቶዋቸዋል:: ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በቀን 26/11/1996 ዓ/ም በተደረገ የቤት ስራ ውል ቤቱን የሚሠሩትን ባለሙያ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ አጠናቀው እንዲያስረክቡ የተዋዋሉ መሆናቸውንና ቤቱም ከተጠሪ ጋር በሀምሌ ወር 1997 ዓ/ም ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት የተጠናቀቀ መሆኑን አንስተው ተከራክረዋል በዚህ ጊዜ ውስጥ ለቤት ግንባታ የተገዙ እቃዎች ያሳያሉ ያሏቸውን የተለያዩ ሰነዶችንም ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ነገር ግን ቤት የተሰራበት ቦታ የተወሰደው በማህበር ስም ነው፡፡ ማህበሩም ይህንን ተጠይቆ ቦታው በማህበር ስም

የተወሰደ መሆኑን ስለመግለፁ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ አገልግሎት በ 29 5/1997 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ እንዲሁም በዚህ ጊዜ የማዕዘን ድንጋይ ተከላ ጥያቄ የቀረበ መሆኑ የማህበሩ አባላት ቤቱን ለመስራት በዝግጅት ላይ ስለሆኑ የመጀመሪያ ዙር ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እንዲለቀቅላቸው ለባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በ 5/6/1997 ዓ/ም ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑ ማህበሩ ለቤቱ ግንባታ የሚሆን ሲሚንቶ ለመግዛት ለሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፐራይዝ ደብዳቤ የጻፈው በ 28/6/1998 እንደሆነ ከባህር ዳር ከተማ አገልግሎት በ 5/11/1999 ዓ/ም ግንባታ መጀመሩን በማረጋገጥ ለግንባታ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ደብዳቤ የተፃፈ መሆኑን አመልካች አንስተው ይህም ቤቱ እንደ ተጠሪ አባባል ሀምሌ 26 ቀን 1996 ዓ/ም ያለመጀመሩን ያሳያል በማለት አጥብቀው ተከራክረዋል። ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት የሚከተሉት ነጥቦች ለትክክለኛ ፍርድ ሲባል ሊጣሩ የሚገባቸው ሆነው አግኝተናል።

1. ክርክር የተነሳበት ቤት የተሠራበት ቦታ በማህበር ስም የተወሰደ መሆኑን ተጠሪ አይክዱም። ይህ ከሆነ በማሕበሩ ስም የተወሰደውን ቦታ አባላት ተከፋፍለዋል ወይስ አልተከፋፈሉም? ተከፋፍለዋል የሚባል ከሆነ ስለ ግንባታው ከተለያዩ አካላት ከተጻፉት ከላይ ከተገለጹት ሰነዶች አንጻር እንዴት ይታያል? በማህበሩ ስም የተወሰደው የቤት መስሪያ ቦታ ካልተከፋፈለና በማህበሩ ስም ቤት የተሰራ ከሆነ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት እሳቸው ከጋብቻ በፊት እንዳሠሩ መከራከራቸው እንዴት ይታያል?
2. ከላይ የተመለከቱት ከተለያዩ አካላት የተፃፉ ሰነዶች ክርክር የተነሳበትን ቤት የሚመለከቱ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚመለከቱ ከሆነ ተጠሪ ቤቱ በሀምሌ ወር 1996 ዓ/ም የተጀመረ ነው የተጠናቀቀውም ከአመልካች ጋር በሀምሌ ወር 1997 ዓ/ም ጋብቻ ከመፈፀማችን በፊት ነው በማለት የሚከራከሩት ክርክር በእውነታ ላይ የተመሠረተ ክርክር ነው ወይስ አይደለም?
3. ግንባታው በማህበሩ ስም የተከናወነ ከሆነ ተጠሪ የግንባታ እቃዎችን በራሳቸው እንደገዙና ቤቱም ከጋብቻ በፊት የተጠናቀቀ ነው በማለት ያቀረቡዋቸው ሰነዶች እንዴት ይታያሉ ?
4. የሚመለከተው አካል በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤትና ቦታ እንደሌለ ለሥር ፍርድ ቤት የገለጸ ከመሆኑ አንጻር ተጠሪ ቦታውን ከቤት የህብረት ሥራ ማህበር ጋር ተከፋፍለው ቤቱን እንደሠሩ መከራከራቸው እንዴት ይታያል? እውነታው ምን ይመስላል?
5. የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂዳት ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ የወሰዱበት ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ/ም ሆኖ የተጠናቀቀ በ 1997 ዓ/ም ነው በማለት የጻፈው ደብዳቤ ከላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት የሰነድ ማስረጃዎች አንጻር እንዴት ይታያል? ከተለያዩ አካላት የቀረቡት ማስረጃዎች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ከሆነ ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ሲባል ፍርድ ቤቱ በተጨማሪ ማስረጃዎች ማጣራት አይጠበቅበትም ወይ? የቀረቡት ማስረጃዎች የተለያዩ ከመሆናቸው አንጻር ማስረጃዎቹን ከሰጡት አካላት ይበልጥ መጣራት አያስፈልግም ወይ? የሚሉትና መሰል ፍሬ ነገሮች ሊጣሩ የሚገባቸው እንደሆነ ተመልክተናል።

የአመልካች ሁለተኛ ቅሬታ ነጥብ በሥላሴ ቅርንጫፍ ኢትዮጲያ ንግድ ባንክ የነበረው ብር 290,889.20/ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሃያ ሳንቲም/ውስጥ ድርሻዬ መወሰን ሲገባው ተጠሪ ከፍቺ ውሳኔ በኋላ

በ 21/3/2008 ዓ/ም ገቢ ያደረጉት ነው ተብሎ መወሰኑ ያለአግባብ ነው ገንዘቡ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ አሜሪካን አገር በትምህርር ላይ በነበሩበት ከየካቲት ወር 2003 ዓ/ም እስከ የካቲት ወር 2005 ዓ/ም ድረስ በየወሩ ሲከፈላቸው ከነበረው ገንዘብ የተጠራቀመ ሲሆን ይህም በቴሌክስ አሜሪካ ሀገር ከሚገኘው ባንክ በ 3/1/2008 ዓ/ም የተደረገውን ተጠሪ በስማቸው በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረጋቸው ብሩን የግላቸው ሊያደርግ አይችልም በማለት በሰበር አቤቱታቸው ላይ አንስተው ተከራክረዋል፡፡የአሁን ተጠሪ ደግሞ አሜሪካን አገር የሄድኩት ለትምህርት እንጂ ሌላ የሚጠራቀም ገንዘብ ለማፍራት አይደለም፡፡ይህ ገንዘብ ለሌላ የሚተላለፍ የሚያውቀኝ ሰው በስሜ የላከው የሌላ ሰው ገንዘብ ነው እንጂ የእኔ እንኳን ቢሆን ፍቺ ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኃላ የሆነን ገቢ አመልካች ለመካፈል የምታቋቁመው ህጋዊ መብት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ከግራ ቀኙ ክርክር ስንነሳ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ተጣርቶ የተሰጠው ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ነጥቦች ማጣራት ያለባቸው ሆነው አግኝተናል፡፡

1.ክርክር የተነሳበት ገንዘብ አሜሪካ ሀገር ከሚገኘው ከየትኛው ባንክ የተላከ ነው? በማን ስም የተጠራቀመ ነው? መቼ የተጠራቀመ ነው? የተላከውስ መቼ ነው?

2.ተጠሪ ይህ ገንዘብ ለሌላ የሚተላለፍ የሚያውቀኝ ሰው በስሜ የላከው የሌላ ሰው ገንዘብ ነው በማለት በዚህ ችሎት ቢከራከሩም ከማን የተላከ ነው?ለማን የተላከ ነው? በአመልካች ስም ለሌላ ሰው ተልኳል ቢባል እንኳ የሥር ፍርድ ቤት ገንዘቡ የተጠሪ ነው ሲል ከሰጠው ውሳኔ አንጻር እንዴት ይታያል?

3.ገንዘቡ ግራቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ተጠሪ በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜ የተጠራቀመና ከፍቺ በኃላ ገቢ የተደረገ ከሆነ ገንዘቡ የጋር ሊሆንና ለአመልካች ድርሻ ሊወሰንላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉና መሰል ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ተጣርተው የተሰጠ ውሳኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አንድ ፍርድ የሚሰጠው የቀረበው ጉዳይ በአግባቡ ከተጠራ በኃላ እንደሆነ ከሥር ሥርዓት ህጉ እንዲሁም ከጉዳዮች አካሄድና አመራር ሥርዓት የምንገነዘበው ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 273 ድንጋጌም ይህንን ያስገነዝበናል፡፡እንዲሁም ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁ.37105 ላይ ይህ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይህ በአንዲ እንዳለ ለፍርድ ቤት የቀረበው ጉዳይ ይበልጥ ማጣራት ያለበት መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች ካቀረቡት ማስረጃዎች በተጨማሪ በሌሎች ማስረጃዎች ማጣራት ያለበት ስለመሆኑ ለፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 264 እና 345 ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት እንመለከታለን፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.23603 – 29861፣13223 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ይህ ትርጉም ደግሞ በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ያለው እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ሶስተኛው የአመልካች ቅሬታ ተጠሪ በብድር የወሰዱትን 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ በተመለከተ ሲሆን ገንዘቡን ከአመልካች እውቅና ውጪ የወሰዱ በመሆኑና እዳውን ከጋራ ገቢ ላይ የከፈሉ በመሆናቸው ከጋራ ገቢ የከፈሉትን

የአመልካችን ድርሻ ሊመልሱ ይገባል በማለት አመልካች የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ገድሞ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ውሏል በማለት ተከራክረዋል፡፡ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሁም በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር እንደተመለከትነው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ሥራ ማህበር ተጠሪ ብር 50,000/አምሳ ሺህ ብር/ሁለት ጊዜ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተበደሩ መሆናቸውን ነው፡፡ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 68 /መ/ መሠረት ከብር 500/ከአምስት መቶ ብር/ በላይ ለመበደር የባልና ሚስት ስምምነት አስፈላጊ መሆኑ የተደነገገ ሲሆን አመልካች ከእኔ ስምምነት ውጪ ተጠሪ የተበደሩት ገንዘብ ነው ይበሉ እንጂ ይህንን ክርክር በማስረጃ አስደግፈው አላስረዱም ፡፡አንድን ፍሬ ነገር ክዶ የሚከራከር ተከራካሪ በማስረጃ ህግ መርህ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 44634 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ በውጭ ሀገር በነበሩበት ጊዜ የተጠሪን ደመወዝ አመልካች በውክልና ሲቀበሉ የብድሩን ገንዘብ ከሚቀበሉት ደመወዝ ላይ ይከፍሉ እንደነበር እንዲሁም አመልካች የማኅበሩ አባል ጭምር እንደሆኑና ስለብድሩ ጠንቅቀው እንደሚያውቁ ለሰበር አቤቶታው በሰጡት መልስ አንስተው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ይህንን በመልስ መልሳቸው በዝምታ አልፈውታል፡፡ በተከራካሪ ወገን የተነሳውን መከራከር ነጥብ በዝምታ ማለፍ አንደማመን እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 83 እና 235 /2/ ይደነግጋሉ፡፡ አመልካች የብድሩን ገንዘብ ተጠሪ ከእኔ እውቅና ውጪ የወሰደና ከጋራ ገቢ ላይ እዳውን የከፈለ በመሆኑ ድርሻዬን ሊመለስ ይገባል በማለት ቢከራከሩም ብድሩ የተወሰደው በትዳር ውስጥ በመሆኑ በህጉ ግምት ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚያስቆጥር ነው፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በብድር ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ለማኅበሩ ሲከፈል የቀረውን ብር 19,540.00 /አስራ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሳኔ አመልካች ያለአግባብ እንደሆነ አንስተው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ውሳኔው ተገቢ እንደሆነ ተከራክረዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ ተጠሪ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሳቸውን ሲያቀርቡም ሆነ በቃል ክርክር ወቅት አንስተው ያለመከራከራቸው የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ ገንዘብ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው የቁጠባ ማኅበሩን ጠይቆ መግለጫ በላከለት መሠረት ነው፡፡ በተከራካሪ ወገን ያልተነሳውን ክርክር መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ይህንን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 182/2/ ድንጋጌ መንፈስና ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የብድር እዳው ሲከፈል ከቀረው ገንዘብ አመልካች ድርሻቸውን ሊከፍሉ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው ቤቱን እና የባንክ ገንዘቡን በተመለከተ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ እንዲሁም ቀሪውን የብድር ገንዘብ ግማሽ አመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ 110235 በቀን 20/10/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኮ/መ/ቁ 202336 በቀን 20/03/2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 14 በተጠሪ ስም የሚገኘው አዲስ ቤት በሥላሴ ቅርንጫፍ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተጠሪ ስም የሚገኘው ብር 290,889.20 / ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሃያ ሳንቲም/የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል።
3. ተጠሪ ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃፊነቱ የተወሰነ የህብረት ሥራ ማህበር በብድር ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ሲከፈል የቀረውን ብር 19,540.00/አስራ ዘጠን ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ ግማሽ አመልካች እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል። ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተቀመጠው መሰረት አመልካች ገንዘቡን መክፈል የለባቸውም ተብሎ ተወስኗል።

4. ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በተመለከተ ከላይ በፍርድ ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 እንዲሁም በስላሴ ቅርንጫፍ ኢትዮጲያ ንግድ ባንክ የተጠራቀመውን ገንዘብ በተመለከተ ከላይ በፍርዱ ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የተቀመጡትንና መሰል ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ አጣርቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲወሰን ብለን በፍትሓብሄር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰንለታል።

5. ሌሎች የውሳኔ ክፍሎች አልተነኩም።

6.የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

7. መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። አስቀድሞ ለተጻፈለት አካል ይጻፍ።

8.የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

መዝገብ ስለተወሰነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የልዩነት ሀሳብ

በቀሪው የውሳኔ ክፍል የተስማማው ቢሆንም ከአሜሪካን አገር ተዛውሮ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሥላሴ ቅርንጫፍ በተጠሪው ስም በተከፈተ ሂሳብ ከፍቼ ውሳኔ በኃላ ገቢ ተደርጉአል የተባለውን ገንዘብ ብር 290,889.20/ ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከሃያ ሳንትም /በተመለከተ ብቻ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አሰፍራለው፡፡

በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በተጠሪው ስም በተለያዩ ባንኮች የተቀመጠው ገንዘብ ተጣርቶ ድርሻቸው እንዲወሰን አመልካቿ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን እና ከላይ በተጠቀሰው ባንክ ገንዘቡ ገቢ መደረጉ የተረጋገጠው የአመልካቿን የዳኝነት ጥያቄ ተከትሎ ለየባንኮቹ ትእዛዝ ተላልፎ በተደረገው ማጣራት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ተጠሪው ተጠቃሹ የባንክ ሂሳብ ደመወዜ የሚከፈልበት ሂሳብ ነው በሚል ከመከራከር በቀር በገንዘብ ዝውውር በሂሳቡ ገቢ የተደረገው ከጋብቻው በኃላ በግል ጥረቴ ያፈራውት የግል ገንዘቤ ነው በሚል ያቀረብኩት ክርክር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም ፡፡ተጠቃሹ ገንዘብ  ተጠሪው ከፍቺ ውሳኔ በኃላ በግል ጥሬ  የፈራሁት ገንዘብ ነው በሚል ያቀረቡት ክርክር ከሌለ ደግሞ ገንዘቡ የፍቺ ክርክር ሲደረግ የሸሸ እና ፍቺ ከተወሰነ ከጊዜ ቆይታ  በኃላ በዝውውር ተልኮ ገቢ የተደረገ ነው ከሚባል በቀር ገቢ የተደረገው ከፍቺ በኃላ በመሆኑ ብቻ የተጠሪው የግል ገንዘብ ነው የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ከፍቺ ውሳኔ በኃላ በአንደኛው ተጋቢ ስም በባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ምንጩ በጋብቻ ጊዜ የተገኘ ገቢ መሆኑን ከማስረዳት በቀር ሌላኛው ተጋቢ የገንዘቡን  ትክክለኛ ምንጭ እንዲያስረዳ ህጉ ግዴታ አይጥልበትም፡፡ተጠሪው ተጠቃሹ የባንክ ሂሳብ ደመወዜ የሚከፈልበት ሂሳብ ነው በሚል ከመከራከር በቀር በዝውውር ገቢ የተደረገው ገንዘብ ምንጩ በጋብቻ ጊዜ የተገኘ ገቢ አይደለም  በማለት  ያቀረቡት ክርክር እስከሌለ ድረስ እንዳመኑ ተቆጥሮ ውሳኔ የሚሰጥበት  ከሚሆን  በቀር  ተጨማሪ ማጣራት ማድረግ  የሚያስፈልግበት ነባራዊ ምክንያት ያለ ሆኖ አላገኘሁም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ላይ «ይህ ገንዘብ ለሌላ ሰው የሚተላለፍ የሚያውቀኝ ሰው በስሜ የላከው  የሌላ ሰው ገንዘብ ነው እንጂ የእኔ እንኳን ቢሆን ፍቺ ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነን ገቢ አመልካች  ለመካፈል የምታቋቁመው ህጋዊ መብት የለም»፡፡ በማለት ተከራክረዋል፡፡እንደሚታየው ከፍቺ ውሳኔ በኃላ ገቢ የተደረገ ነው ከማለት በቀር ገንዘቡ ከፍቺ ውሳኔ በፊት የተገኘ  ገቢ ስለመሆኑ በሰበር ደረጃም ቢሆን ተጠሪው  አልካዱም፡፡ግራቀኙ አሁንም  በንብረት  ክርክር ላይ በመሆናቸው ከፍቺ ውሳኔ በኃላ  ሁለት ዓመት ማለፉ አመልካቿን የጋራ ንብረት ለመካፈል  የሚከለክል አይደለም፡፡ ገንዘቡን ሌላ ሰው  በስሜ  የላከው ነው ከማለት በቀር የተላከው ከማን እና ለማን  እንደሆነ የተላከለት ነው በተባለው ሰው ስም በቀጥታ ሊላክ  ያልቻለው በምን ምክንያት  እንደሆነ እና ለሌላ ሰው የተላከ ነው የሚሉትን ገንዘብ በሂሳባቸው ያቆዩበት በምን ምክንያት እንደሆነ ተጠሪው የገለጹት ነገር ካለመኖሩም በላይ የዚህ ዓይነት ክርክር በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ  ክርክር በመሆኑ በፍታሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329 ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም፡፡ ግራቀኙ በሚከራከሩበት ገንዘብ ላይ እስካሁን ባለው ሂደት የይገባኛል ጥያቄ ያቀረበ ሶስተኛ ወገን ስለመኖሩም የመዝገቡ ግልባጭም ሆነ የተጠሪው የሰበር ክርክር  የሚጠቁሙት ነገር የለም፡፡

በመሆኑም ተጨማሪ ማጣራት ማድረግ ሳያስፈልግ ከአሜሪካን አገር ተዛውሮ በኢትዮጱያ ንግድ ባንክ ስላሴ ቅርንጫፍ በተጠሪው ስም በተከፈተ ሂሳብ  ከፍቺ ውሳኔ በኃላ ገቢ ተደርጎአል የተባለውን  ገንዘብ ብር 290,889.20/ሁለት መቶ

ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ከሃያ ሳንቲም/ግራቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በቀጥታ ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት።

ማ/አ